## የአነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዝ ፋይናንስ ፕሮጀክት ዳራ

### *በፕሮጀክቱ ለአነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች የሚሰጡ ዋና ዋና የድጋፍ ዓይነቶች፡-*

- *የካፒታል ዕቃ ኪራይ አቅርቦት / Capital goods lease finance/*
- *የሥራ ማስኬጃ ብድር /Working capital loan/*
- *የንግድ ሥራ ልማት አገልግሎት /Business development services/*

የአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ዘርፍ እድገት ወደ ኢንዱስትሪያላይዜሽን ለሚደረግ ሽግግርና ኢንዱስትሪ መር ጠንካራ የሀገር ኢኮኖሚ ለመገንባት ወሳኝ ሚና አለው፡፡

በዘርፉ የገቢ ተኪ (Import substitute) እና ወጪ (Export) ምርቶችን በማበረታታት የውጭ ምንዛሪ የማዳንና የማስገኘት ጥረት በመንግስት በኩል ከፍተኛ ትኩረት የሚሰጠው ነው፡፡ ከዚህም በላይ የዘርፉ ዕድገት ዘላቂ የስራ ዕድል ምንጭ በመሆን የዜጎችን አይነተኛ ተጠቃሚነት የሚያረጋግጠው የማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ በመንግስት በኩል ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶታል፡፡

ቀደም ሲል የፌዴራል አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ማስፋፊያ ባለስልጣን በመባል ይጠራ የነበረውና አሁን የኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት የሚል ስያሜ ያገኘው ተቋም በሁሉም ክልሎችና በሁለቱ የከተማ አስተዳደሮች ካሉት መዋቅሮቹ ጋር ለዘርፉ ዕድገት ውጤታማነት የበኩሉን ጥረት እያደረገ ይገኛል፡፡ በዘርፉ ከሚደረጉ ድጋፎች ውስጥ የአነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዝ ፋይናንስ ፕሮጀክት ትግበራ ይገኝበታል፡፡

ፕሮጀክቱ በዘርፉ እድገት ላይ ቀጥተኛ ተጽዕኖ ከሚያሳድሩ ተግዳሮቶች ውስጥ ዋነኞቹ የካፒታል እጥረት፣ የቴክኖሎጂ እና የንግድ ስራ እውቀት ውሱንነት መሆኑን በመገንዘብ፤ በዋነኝነት ለአነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች የፋይናንስ ተደራሽነት በማሳደግ ያለባቸውን የፋይናንስ እጥረት የመቅረፍና የንግድ ስራ አገልግሎት ስልጠናን የመስጠት ዋነኛ ዓላማን በመተለም የተነደፈ ነው፡፡

የፕሮጀክቱ ጽንሰ ሃሳብ የመነጨው እንደ አውሮፓውያን ዘመን አቆጣጠር በ2014 ዓ.ም በኢትዮጵያ አነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች ፋይናንስ አቅርቦት ዙሪያ በዓለም ባንክ ከተደረገ ጥናት ሲሆን፣ ጥናቱ ጥቃቅን ኢንተርፕራይዞች በማይክሮ ፋይናንስ በኩል የብድር አቅርቦት ተጠቃሚ እንደሆኑና፣ ትላልቅ ኢንተርፕራይዞች ደግሞ በባንኮች በኩል የብድር አቅርቦት የሚያገኙ መሆናቸውን ይጠቁማል፡፡ በዚሁ መሰረት በመካከል የሚገኙ በጥናቱ “Missing middle’’ የሚል መጠሪያ የተሰጣቸው አነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች የብድር አቅርቦት ችግር ያለባቸው መሆኑ ተለይቷል፡፡ በዚህ መነሻነት በጥናቱ እንደመፍትሄ ሃሳብ የቀረበው፤

ሀ. የማይክሮ ፋይናንሶችን አቅም በገንዘብና በስልጠና በማጎልበት የብድር አቅርቦት ስራቸውን ከፍተኛ የብድር ፍላጎት ወዳለበት ወደአነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች ትኩረት እንዲያደርጉ ማድረግ፣

ለ. የንግድ ባንኮችም የብድር አሰጣጥ ፖሊሲያቸውን በመፈተሽ ከትላልቅ ኢንተርፕራይዞች የፋይናንስ ድጋፍ በተጨማሪ ዝቅ ብለው አነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞችን የመደገፍ አካሄድ ላይ እንዲያተኩሩ፤ ይህም አሰራራቸው አሁን ያለውን የአነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች የብድር ፍላጎት መሰረት ያደረገ እንዲሆን ይጠቁማል።

በዚህ ጥናት መነሻነት የአነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች ፋይናንስ ፕሮጀክት የኢትዮጵያ መንግስትና የዓለም ባንክ ባደረጉት ስምምነት እውን ተደረገ። በዚህም መሰረት የብድር ውል ስምምነቱ በኢትዮጵያ መንግስትና በዓለም ባንክ መካከል እ.አ.አ ሰኔ 15 ቀን 2016 ዓ.ም ተፈረመ።

ገንዘብ ሚኒስቴር የኢትዮጵያ መንግስትን በመወከል የብድሩ ዋና ፈራሚ ሲሆን ፕሮጀክቱን የማስፈጸም ኃላፊነት ለኢትዮጵያ ልማት ባንክ እና በቀድሞ ስሙ የፌዴራል አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ማስፋፊያ ባለስልጣን ለአሁኑ የኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዞች ልማት በውክልና ሰጥቷል። በዚህ ተቋም ስር የሚገኘው የፕሮጀክት ማስተባበሪያ ጽ/ቤት አጠቃላይ የማቀናጀት ሚና እንዲሁም በሁለተኛው፣ ሶስተኛውና አራተኛው የፕሮጀክት አካላት /Components/ ላይ ቀጥተኛ የማስፈጸም ኃላፊነት ተሰጥቶታል።

ቀደምሲል የፕሮጀክቱ ማስተባበሪያ ጽ/ቤት ተቋቁሞ እንቅስቃሴ የጀመረው በኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ውስጥ የነበረ ሲሆን ከዓለም ባንክ ጋር በተደረገው ስምምነት የመዋቅር ለውጥ በመደረጉ በአሁኑ ወቅት ፕሮጀክቱ በኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት ስር ቢሮ ከፍቶ ስራውን ሲያከናውን ቆይቷል።

**የፕሮጀክቱ ጠቅላላ በጀትና ምንጮ፡-**

ለፕሮጀክቱ የተበጀተው ጠቅላላ የገንዘብ መጠን 276 ሚሊዮን የሜሪካ ዶላር ሲሆን፣ ከዚህም ውስጥ 200 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር ከዓለም አቀፍ ልማት ማህበር /IDA/ ሲገኝ ቀሪው 76 ሚሊዮን ዶላር ደግሞ ከአውሮፓ ኢንቬስትመንት ባንክ /EIB/ የተገኘ ነው።

የዋና ፕሮጀክቱ አራት ዋና ዋና ኮምፖነንቶች ከ2017 አጋማሽ እስከ ነሐሴ 2021 ድረስ ሲተገበር የቆየ ሲሆን በ2020 በዓለም አቀፍ ደረጃ በተከሰተው የኮቪድ 19 ወረርሽኝ ምክንያት በአነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች ላይ የፈጠረውን ጫና ከግምት ውስጥ በማስገባት የዓለም ባንክ ተጨማሪ ፋይናንስ (Additional Finance) 200 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር በመፍቀድ ፕሮጀክቱ ለተጨማሪ ሦስት ዓመታት እንዲራዘም ተደርጓል።

**የፕሮጀክቱ ተጠቃሚዎች**

የፕሮጀክቱ ተጠቃሚዎች የተቀመጡትን መመዘኛዎች የሚያሟሉ አነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች ሲሆኑ በማኑፋክቸሪንግ፣ በግብርና ምርቶች ማቀነባበሪያ፣ በግንባታ ግብዓት ማምረትና በቱሪዝም ዘርፎች የተሰማሩ ናቸው።

**የፕሮጀክቱ የትግበራ ጊዜ**

የዋና ፕሮጀክቱ የትግበራ ጊዜ አምስት ዓመታት (እ.ኤ.አ. ከ2017 – 2022) የነበረ ሲሆን የተጨማሪ ብድሩ ሶስት ተጨማሪ ዓመታት (እ.ኤ.አ. ከ2022 – 2025) የማስፈጸሚያ ጊዜ ይኖረዋል፡፡